**ምስጋናና ውዳሴ** (Thanks giving and praise).

**ምስጋና፡ -**

**መዝ 95፡1-6፣ የምስጋና፣ ውዳሴና አምልኮ (Thanks giving, praise and worship) ቅደም ተከተልን ያሳያል፡- ምስጋና-ውዳሴ- አምልኮ** (በምስጋና ይጀምርና ወደ ውዳሴ በመሻገር በመጨረሻ ወደ አምልኮ እንደ ሚገባ ያመለክታል)፡፡

ለምስጋና ሁለት የዕብራይስጥ ቃላት አሉ፡፡ **1ኛ. ያዳህ** ሲሆን፡- (መዝ 100፡1-5፤ 1ዜና 16፡34-35፣) **2ኛው. ተውዳህ** ነው፡፡ ያዳህና ተውዳህ "ያድ/እጅ" ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል የመጡ፣ እጅን ወደ ላይ በማንሳት ወይም ወደፊት በመዘርጋት ማመስገንን/ማወደስን የሚያመለክቱ ናቸው፣ ዕዝ 3፡11፣

ምስጋና፡- በዝማሬም ሆነ ያለ ዝማሬ ድምጽ በማውጣት በሙዚቃ መሳሪያዎች በማጀብ ጭምር የሚገለጽ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለሕዝቡ መልካምና ባለብዙ ውለታ፣ እንደ እርሱ ያለ ማንም የሌለ መሆኑን እውቅና የሚሰጥበት ነው፡፡ የምስጋናችን ምክንያት እግዚአብሔር በግልም ሆነ በወል ስላደረገልን መልካም ነገር፣ ስለዋለን ውለታ እያደረገልን ስላለውና ወደፊት ስለሚያደርግልን ብዙ ነገር ሁሉ ምላሽ የምንሰጥበት ነው፡፡ የውለታው ብዛት ለመጥቀስ ያህል፡- ምድርና ሞላዋን፣ ጸሃይና ጨረቃን፣ በምድር ላይና ውስጥ ያሉት ፍጥረታት ሁሉ ሰርቶ ለሰው መጠቀሚያ እንዲሆን በነጻ በመስጠቱ እናመሰግነዋለን፣ እነዚህን ፍረጥረታት ሁሉ ስለ ፈጠረበት ታላቅ ዕውቀቱ ችሎታውና ጥበቡ እናወድሰዋለን፡፡

ስለመገበን፣ ስላጠጣን፣ ስላለበሰን፣ መጠለያ ስለሰጠን፣ ዕውቀትና የመማር አቅም፣ የማስታወስ ችሎታ፣ የመስራት ችሎታ፣ ሙሉ የሰውነት አካል ክፍሎችና ጤንነት ስለ ሰጠን፣ ከጨለማው ኃይላት ጥቃትና ከተለያየ አደጋ የሚጠብቀን ጋሻችን ስለሆነ...ወዘተ ሊመሰገን ይገባዋል፡፡

በምድር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ የተለየ ክብር ለሰው መስጠቱ፣ ስለ ሚያናገረን፣ በኛ ሰለሚኖር የኛም መኖሪያ ስለሆነን፡ ሰላማችን፣ ደስታችንና ዕረፍታችን በርሱ ስለሆነ በምስጋና ላይ ምስጋና ልናበዛ ይገባል፡፡

ስለ ዘላለማዊ ምህረቱ፣ ፍቅሩ፣ ቸርነቱ፣ ትዕግስቱ፣ ጸጋው፣ ርህራሄው፣ ጻድቅ ፍርዱ፣ ፈዋሽነቱ፣ በየትውልዱ በቁጥር እያበዛን መሆኑ፣ ስለቤተሰባችን አባላት፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ሰጠን ታላቅ መዳን፣ ለወደፊት ስላዘጋጀልን ዘላለማዊ ህይወት፣ በእድሜያችን አንድ ቀን ቀርቶ አንድ ሰዓት እንኳ ያለርሱ ዕርዳታ/ውለታ ያለፍነው ስለሌለ እናመሰግነዋለን፤ (1ተሰ 5፡18፣ መዝ 139፡13-14፣ 34፡1)

የምስጋናችን ምክንያት በወቅቱ ያለንበት ሁኔታ የተመቻቸ መሆን አለመሆን ላይ ብቻ ሳይወሰን እግዚአብሔር እኛን ለማዳን ያደረገውና የሆነውን እንዲሁም መልካም ባህርያቱን ሁሉ ከማሰብ የተነሳ ነው፡፡ ይሄ ብቻውን እርሱን ለማመስገን፣ ለማወደስና ለማምለክ ከበቂ በላይ ምክንያት ነው፡፡ የማይመች ነገር በገጠመንም ጊዜ ለበጎ እንዲሆን ስለሚለውጠው ማመስገን፡፡ እርሱ ለጊዜው በአንዳንድ ምክንያቶች ኑሮዋችን ስራችን፣ ጤናችን ... ምቹ ስላልሆነ አይለዋወጥም፡፡ (መዝ 100፡5፣ ኤር 33፡11፣ ኤፌ 5፡20)

ሰው ያለውና የሚኖረው መልካም ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር የተቀበለውና የሚቀበለው ሲሆን እኛ ለእግዚአብሔር በቀጥታ የምንሰጠው ብቸኛ ነገር በምስጋናና ውዳሴ ማክበር ነው፡፡

ከልብ ማመስገንና ማወደስ በእግዚአብሔር ፊት ያማረ መስዋዕት እንደ ማቅረብ ነው፡፡ (መዝ 107፡2፣ 69፡30-31 ዕብ 13፡15)

**ውዳሴ** (Praise)

"ውዳሴ" ለሚለው ቃል ከ8 በላይ የዕብራይስጥ ቃላት አሉት፡፡ እነዚህ የዕብራይስጥ የውዳሴ ቃላት ማወቅ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሲጠና ስለ ውዳሴ የሚናገሩ ጥቅሶች፣ በአማርኛ ምስጋና ተብለው የተተረጎሙ ስላሉ በዕብራይስጥ በተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ቃላቱን ማገናዘብ ሲፈለግ የውዳሴ ቃል መሆኑን ለመለየት እንዲረዳ ነው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት፡፡

1. **ተሂላህ** - መዝ 22፡3፣9፣ 33፡1፣ ኢሳ 61፡3፣ (celebration with songs, shouts and holy noise) 2. **ሃላል** የብዙ ቁጥሩ ሀሌል (ሀሌሉ + ያህ = ሀሌሉያህ ለሚለው ስርወ-ቃል ነው፣) - መዝ 113፡1-3፣ 149፡3፣ 150፡1-3፣ 3. **ያዳህ** - መዝ 63፡1፣ 107፡15፣ (ያድ ማለት እጅ ማለት ነው፣ እጆችን ወደፊት በመዘርጋት ማወደስ)፡፡ 4. **ተውዳህ** - መዝ 50፡14፣ 23፤ እጅ ወደላይ በማንሳት ማወደስ፡፡ በዘጸዓት 17 ላይ ሙሴ እጆቹን ባነሳ ጊዜ አማሌቃውያን ይሸነፉ እንደ ነበር፡፡ እግዚአብሔር እጃችንን በማንሳት (ለእርሱ እጃችንን በመስጠት እንዲገዛን በራሳችን ላይ በመሾም) ስናወድሰው ጠላቶቻችንን ይዋጋል)፡፡ 5. **ሻባች** means to to shout, to command, to address in loud tone. (በእግዚአብሔር ታላቅ ኃይል መተማመንን የሚገልጽነው) መዝ 47፡1፣ 145፡4፣ 6. ባራክ (መባረክ/መንበርከክ) ትህትናን ለመግለጽ- መዝ 89፡52፣ 95፡6፣ 1ነገ 18፡42፣ 1ዜና 29፡20፣ 34፡1፣ 7. **ዛማር** - መዝ 21፡13፣ 47:6, 1ዜና 16፡9 (praising with string instruments), 8. ካራ (የዳዊት ዳንስ) 2ሳሙ14፣ 9. ታኬያ፣ መዝ 47፡1 እጆችን በማጨብጨብ፡፡

መዝ 150፡1-5፣ እግዚአብሔርን በመቅደሱ አወድሱት፤ በታላቅ ጠፈሩ አወድሱት ለኃያል ስራው አወድሱት፣ ከመታወቅ በላይ ለሆነው ታላቅነቱ አወድሱት,...፡፡ (ማሳሰቢያ፡- የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ከ1-5 ባሉት ቁጥሮች ሁሉ በእያንዳንዱ ጥቅስ ሁለት ጊዜ አወድሱት ይላሉ) (መዝ 48፡1፣ 90፡2፣ 145፡3፣)

ይህ መዝሙር ለአምላካችን ውዳሴ ለማቅረብ መነሻ የሚሆኑን ነገሮችን በመጥቀስ ወሰን የሌለው ታላቅ ማንነቱና ሥራው በማነሳሳት ማወደስ፣ ማሞገስና፣ ማድነቅን እንድንችል የሚያግዝ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ዙፋን ያለበት መቅደስ የተላበሰው ድንቅ ውበት፣ በሁሉም አቅጣጫ ወሰን የሌለው ሰፊ ጠፈርን፣ በታላቅ ኃይሉ በጠፈር ሰርቶ ያስቀመጣቸው እጅግ ግዙፍና ተቆጥረው ሊያልቁ የማይችሉ ከዋክብት፣ ፕላኔቶች፣ ጨረቃዎች ...ወዘተ፣ በመዘርዘር ማድነቅ ነው፡፡

- ውዳሴ በዝማሬም ሆነ ያለዝማሬ በንግግር ድምጽ በማውጣት (በሙዚቃ መሳሪያዎች በማጀብ ጭምር) የሚገለጽ ነው፡፡ ለእግዚአብሔር ማንነት ሁሉና ለሥራው ታላቅነት እውቅናና ክብር የምንሰጥበት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ማንነትና የሰራው ስራ ታላቅነት የቻሉትን ያህል ዘርዝሮ በማነሳሳት የሚገለጽ ነው፡፡ (ይህ ሲባል ግን እግዚአብሔር የሰራው ስራና የፈጠረው ፍጥረት ዓይነትና ብዛት ታላቅነት ጥቂቱን ለመጠቃቀስ ያህል ነው እንጂ ተዘርዝሮ የማያልቅ መሆኑን ኢዮ 26፡4-14 ያስረዳል፡፡
  በሌላ በኩል ደግሞ የምንሰማቸው የመንፈሳዊ ዝማሬዎች ይዘት በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ (የእምነት፣ የንስሃ፣ የጸሎት፣ የማበረታቻ) ስለሆነ ዝማሬ ሁሉ እግዚአብሔርን የሚያወድስና የሚያመሰግን እንዳልሆነ የሚታወቅ ነው፡፡ የምስጋናና ውዳሴ መዝሙሮች ሲዘመሩ ሌሎች መዝሙሮች ከሚዘመሩበት ጊዜ ይልቅ እግዚአብሔር ክብሩን የሚገልጡ ኃያል ሥራዎች ስለሚሰራ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት በዛ እንዲሉ ማድረግ የተሻለ ነው፡፡

  ውዳሴ የእግዚአብሔርን ኃይል፣ ጥበብ፣ ማስተዋል/ዕውቀት፣ ችሎታ፣ ስልጣን፣ ብልጽግና፣ ለጋስነት፣ ፍቅር፣ ምህረትና የሁሉም ባሕርያቱ ታላቅነት በማነሳሳት የሚያደንቁበት ነው፡፡
  በሰማይ ያኖራቸው ከዋክብትና ፕላኔቶች፣ ጨረቃዎች፣ ግዝፈትና ከመታወቅ በላይ የሆነ ብዛት፣ በፈጠራቸው ፕላኔቶችና በህዋው ውስጥ የፈጠራቸውና ያኖራቸው የሚታዩና የማይታዩ ፍጥረታት ብዛትና፣ ዓይነት፤ በያንዳንዱ ኮከብና ፕላኔት ውስጥ ያስቀመጠው ኃይል...ወዘተ ታላቅነት የሚዘረዘርበት ነው፡፡

  የፈጠራቸው ሰዎችና ትውልድ ብዛት፤ ሰዎችን ለማዳን የሰራው ሥራ ታላቅነት፣ ወደፊት ለሰዎች ሊያደርገው /ሊያወርሰው/ ያለው ርስት... ታላቅነት እያነሳሱ የሚያወድሱበት፣ የሚያሞግሱበትና የሚያደንቁበት ነው፡፡

**እግዚአብሔርን ከምናወድስበትና ከምናመሰግንበት ምክንያቶች ለመጥቀስ ያህል፡ -**

1) ውዳሴ የተገባው ስለ ሆነ (worthy of it, deserves it፣): - 1ዜና16፡25-29፣ መዝ 145፡3፣ ራዕ 5፡12-13፤

2) ሁሉም የምናየው የምንዳስሰው፣ የሚጠቅመን ነገር፣ የሚታየውም የማይታየውም ፍጥረት የተሰራው/የተፈጠረው በእርሱ ስለሆነ፡፡ መዝ 92፡4-5፣ 104፡24፣ 111፡2-4፣ ኢዮ 5፡9

3) በፍጥረት ሁሉ ላይ ሙሉ ኃይልና ሥልጣን የእርሱ ስለሆነ 1ዜና 29፡11፣ ራዕ 5፡13፣ መዝ 8፡ 3-8
4) የተፈጠርንበት ምክንያት እርሱን ለማመስገን፣ ለማወደስና ለማክበር ስለሆነ፡፡መዝ 102፡18፣ 1ጴጥ 2፡9

ኢሳ 43፡21፣ ውዳሴዬን/ታላቀነቴን ያውጅ ዘንድ ለራሴ ያበጀሁት ህዝብ፡፡

ኢሳ 43፡7 በስሜ የተጠራውን ሁሉ፣ ለክብሬ የፈጠርሁትን ያበጀሁትና የሰራሁትን አምጡ፡፡

5) መዝ 19፡1-6፣ እንደበት የሌለውና ለእኛ ጥቅም የተፈጠረ ፍጥረት ሁሉ የእርሱን ታላቅነት ሲናገር እኛ ዝም ማለት ስለ ሌለብን፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃ 19፡37-40 ደቀ-መዛሙርቴ ዝም ቢሉ ድንጋዮች ይጮሃሉ እንዳለው እኛ ዝም ብንል ተፈጥሮ ስለ አምላካችን ታላቅነት መናገሩን ሳያቋርጥ ስለሚቀጥል፡፡

## የማመስገንና የማወደስ ጠቀሜታ

1. ለእግዚአብሔር በጉዳያችን ጣልቃ ገብቶ ማዳኑን የሚያሳይበት፣ ጠላትን የሚመታበት መንገድ ይከፍታል፡፡ መዝ 50፡23፣ 2ዜና 20፡21-22፣ ሐሥ 16፡25-26
መዝ 22፡3፣ ምስጋና ማቅረብ ለምንጠራው ጌታ ዙፋን ማዘጋጀት ነው፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ስለሆነ ብቻ የሚያስፈልገንን ሁሉ አያደርግም፡፡ የኛ ድርሻ እንዲኖር በተደረገበት ሁኔታ ሁሉ ትንሹን ነገር በማድረግ፣ ማለትም ምስጋናና ውዳሴን በማቅረብ ድርሻችንን መወጣት አለብን፡፡

መዝ 8፡2፣ "ከህጻናትና ጡት ከሚጠቡት አፍ በሚወጣ ምስጋናና ውዳሴ አማካይነት ጠላትና ለበቀል የወጣውን ጸጥ የሚያሰኝ ኃይል አዘጋጀህ፡፡"

መዝ 149፡5-9፣ "የአምላክ ውዳሴ በአንደበታቸው፣ ባለ ሁለት ልሳን ሰይፍ በእጃቸው ይሁን፡፡ በዚህ ህዝቦችን ይበቀላሉ፤ ሰዎችንም ይቀጣሉ፡፡ ነገስታቶቻውን በሰንሰለት መኳንንቶቻቸውን በእግር ብረት ያስራሉ፡፡ (በእነርሱ ላይ የሚሰሩት አለቃ መናፍስትን ለማለት ነው፡፡) ይህም በነርሱ ላይ የተጻፈውን ለመፈጸም ነው፡፡ ለቅዱሳኑ ሁሉ ይሄ ክብር አላቸው፡፡" ይሄ ምስጋናና ውዳሴ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በአንድነት ስንጠቀም ያለው ጠቀሜታን ያሳያል፡፡
2. ምስጋናና ውዳሴ የመከባበድን/የመጫጫንን መንፈስ የምናጠቃበት መሳሪያችን ነው፡፡ 1ሳሙ 16፡ 23
3. መዝ 2፡2-4፣ ውዳሴ እግዚአብሔር እንደሚያይ እንድናይ ይረዳናል፡፡ በእግዚአብሔር እይታ የጠላት ኃይል ትንሽ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ትልቅነት እያየን እንድንቆይ ይረዳናል፡፡ ጌታ እየሱስ ዓለምን ገና ድሮ ስላሸነፈ ምን ይመጣ ይሆን ብሎ አይሰጋም፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ምን ጊዜም ከከበረ ዙፋኑ የሚነቀንቀው የለም፡፡ ጠላታችንን ወይም የደረሰብን ችግር አግንነን በማየት ፈንታ ትክክለኛ አስተሳሰብና የአእምሮ ሰላም እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ ችግራችን/የገጠመን ሰልፍ ዝቅ ያለ/ትንሽ መሆኑን እናውቀዋለን፡፡ 1ሳሙ 17፡45 ዳዊት የጎልያድን ግዙፍነት የያዘውም የውጊያ መሳሪያ ጠንካሬ አልካደም፡፡ ከዚህ ሁሉ ግን እግዚአብሔር ይበልጣል ብሎ በእግዚአብሔር ተማምኖ ጎልያድን ውጊያ ገጥሞ አሸንፏል፡፡ ዮሐ 16፡33 "..በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፣ ነገር ግን አይዟችሁ (ደስ ይበላችሁ/በርቱ)፣ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ"

4. አእምሮ በሌላ ሰው አግባባዊ ባልሆነ ድርጊት ወይም በተለያዩ ነገሮች ማሰብ ሲጠመድ ከዚያ በመውጣት ለመንፈስ ቅዱስ ስራ ራስን ለማመቻቸት ይጠቅማል።
2 ነገ 3፡14-15፣ ኤልሳዕም እንዲህ አለው፤ "የማገለግለው ሕያው እግዚአብሔርን፣ የይሁዳን ንጉሥ

ኢዮሣፍጥን ባላከብር ኖሮ፣ አንተን አላይም ወይም ጉዳዩ አልልህም ነበር:: [15] አሁንም ባለ በገና አምጡልኝ::" ታዲያ ባለ በገናው በሚደረድርበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔር እጅ በኤልሳዕ ላይ መጣ፤

5. እግዚአብሔር በሚያወድሰው ሕዝብ ደስ ይሰኛል፡፡ ደስ ሲሰኝ ደግሞ የሕዝቡን ጠላቶች ለመምታት ኃያል ክንዱን እንዲያነሳ ያስችላል፡፡ በስሙ የተጠሩት ሕዝቡ እርሱን በማወደስ በሁሉም ጉዳያቸው በእርሱ ጸጋ የሚደገፉ መሆናቸውን በመግለጽ ራሳቸውን ዝቅ ሲያደርጉ/ትሁታን ሲሆኑ በማዳኑ ሙላት ይባርካቸዋል፡፡ መዝ 149፡1-4
6. ውዳሴና ምስጋና ወደ እግዚአብሔር መገኘት/ህልውና ወዳለበት በር ለጸሎት የምንደርስበት ነው፡፡ ያለ እነርሱ ገብቶ ልመናን ማቅረብና በምልጃ ጸሎት ማገልገል የተፈቀደበት ሁኔታ የለም፡፡ መዝ 95፡2፣ ኢሳ 60፡18፣

ባለማመስገን ህይወት ውስጥ ያሉ ሰዎች የእያደር የሚገቡት በማጉረምርምና በማማረር ጎዳና ውስጥ ነው፡፡ ምላስ የተሰጠን እንድናመሰግንበት ነው፡፡ ላልተሰጠበት ዓለማ ማዋል ስለሌለብን፡፡ ሮሜ 1፡21-22፣ 2ጢሞ 3፡1-2

***<u>መቼ ነው/ምን ያህል ጊዜ</u> ነው እግዚአብሔርን ማመስገንና ማወደስ ያለብን፡፡*** መዝ 34፡1፣

1. መዝ145፡2 "በየቀኑ እባርክሀለሁ፣ ስምህን ከዘለዘላለም እስከዘላለም አመሰግናለሁ፡፡"
2. መዝ 35፡25 "አንደበቴ ጽድቅህን፣ ምስጋናህንም ቀኑን ሙሉ ይናገራል፡፡"
3. መዝ 34፡1 "እግዚአብሔርን ሁልጊዜ አከብረዋለሁ፣ ምስጋናውንም <u>ዘወትር</u> ከአፌ አይለይም፡፡" ዕብ 13፡15 "ስለዚህ <u>ዘወትር</u> የምስጋናን መስዋእት ይኸውም ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮች ፍሬ በኢየሱስ አማካይነት ለእግዚአብሔር አቅርቡ፡፡" ዘወትር የሚለው ቃል continually የሚል ስለሆነ ሳይቋረጥ መሆን እንዳለበት የሚያመለክት ነው፡፡
4. ኤፌ 5፡20 "...እግዚአብሔር አብን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም <u>ስለ ሁሉ ነገር</u> ሁልጊዜ አመስግኑ፡፡" በተመቻቸ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በመከራም ጊዜ እግዚአብሔር ለበጎ ስለ ሚለውጠው አመስግኑ፡፡ 1ተሰ 5፡16-18፣ "ሁል ጊዜ ደስ ይበላችሁ፣ በማናቸውም ሁኔታ አመስግኑ፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ለእናንተ ይህ ነውና፡፡"
5. መዝ145፡21 "አፌ የእግዚአብሔርን ምስጋና ይናገራል፣ ፍጡር ሁሉ ከዘላለም እስከዘላለም ቅዱስ ስሙን ይባርክ፡፡"

ሁሉ ቀን የምንጸልይበት ሰዓት ሊረዝም ሊያንስ ይችላል፡፡ ግን ለአንድ ሰዓትም ቢሆን የምንጸልይ ከሆነ ማመስገን አለብን፡፡ እየጸለይን ባልሆነበት ጊዜም ቢሆን ማመስገንና ማወደስ ተገቢ ነው፡፡

***<u>ማን ያመስግን፡-</u>*** "እስትንፋስ ያለው ሰው ሁሉ (ካልሞተ በስተቀር) ያመስግን/ያወድስ፡፡" መዝ 150፡6

***<u>እንዴት እናመስግን፡-</u>*** በውዴታ/በፈቃደኝነት፣ ከልብ በመነሳሳት/በመነቃቃት፣ በእርካታ/በማስተዋል፣ መዝ 63፡5

***በምን ሁኔታ (ሜተድ) ማመስገንና ማወደስ፡-*** ደስታ በተሞላ አፍና ከንፈር ቃል፣ በዝማሬ ከአካል ውዝዋዜ/ዳንስ ጋር፣ እጆችን ወደፊት በመዘርጋትና ወደላይ በማንሳት፣ በመቆም፣ በመንበርከክ....፡፡ መዝ 81፡1፣ 100፡2

***የምስጋናና ውዳሴ መዝሙሮች ሲዘመሩ አንዳንዴ የሚሰሙና መወገድ ያለባቸው ነገሮች፡-***

1. እነርሱም፣ "ቃላት አጣሁ"፣ "ቃላት ባገኝሁ ኖሮ"፣ "ምን ልበልህ"፣ " (መውደዴን) በምን ልግለጠው" ምነው በኖረና ፍቅሬን ምገልጥበት... ወዘተ የሚሉ ሀረጎችና አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ እግዚአብሔር የሌሉን ቃላትና ሐረጎች ወይም ማናቸውም ነገሮች ከእኛ አይጠብቅም፣ እርሱ ልባችንና ድርጊታችንን ስለሚያውቅ እንደዚህ ስላልነው በጣም ይወዱኛል አይልም፡፡ በሕይወታችን ቃሉን በመተግበር/በመታዘዝ ረገድ ጥቂት እንኳ ያልተራመድን ሆኖ ሳለ እንደዚህ ዓይነት አባባሎች መደጋገም እግዚአብሔርን ጎሽ ከሚያሰኝ ይልቅ ለመሸንገል እንደ መሞከር ይሆናል፡፡ እግዚአብሔርን መውደዳችን የሚታወቀውና የሚገለጸው ፈቃዱን በማድረግ መልካም ፍሬ በማፍራት ማደግ ነውና (ዮሐ 14፡21፣ 23፣ 15፡8)

2. በዝማሬዎች ውስጥ እግዚአብሔርን 1ኛ፣ 2ኛ፣ እያሉ በቁጥር ደረጃ በመስጠት ማወደስ አግባብነት የለውም፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር 1ኛ፣ 3ኛ፣ 100ኛ… ወዘተ ተብሎ የሚወዳደረውና የሚመሳሰለው የሌለ፣ እርሱ ብቻውን እውነተኛ አምላክ የሆነ ሲሆን ሌላው ሁሉ ግን የእርሱ በጎ ፈቃዱ ሆኖ የፈጠረው ፍጥረት በመሆኑ፡፡ ኢሳ 40፡18፣ 25፣ 46፡5፣ 9፣ ዘጸ 9፡14፣ ዘዳ 33፡26፣ መዝ 89፡6፣

3. የዝማሬ አገልግሎት የሚካሄደው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት እስከ ሆነ ድረስ ይበልጥ ትኩረት መስጠትና በዛ ማድረግ የሚገባው ግጥሞቹ በምስጋና ተጀምረው በምስጋና የሚያበቁና በውዳሴ ተጀምረው በውዳሴ የሚያበቁ ቅልቅል ያልሆኑ መዝሙሮች ላይ ቢሆን መልካም ነው፡፡ ይህ ማለት ግን የጸሎት፣ የእምነት፣ የንስሃ፣ ከበዓል ቀናት ጋር የተያያዙ…. ወዘተ መዝሙሮች አያስፈልጉም ለማለት አይደለም፡፡

©ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር)                    2018 ዓ.ም.